# ስለ መጽሃፍ ቅዱስ

በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ 66 መጻሀፍት አሉ። እነዚህም መጻሀፍት ለሁለት ይከፈላሉ። አንደኛው የብሉይ (አሮጌው) ኪዳን ሲሆን ፤ ሁለተኛው ደግሞ አዲስ ኪዳን ነው። የብሉይ ኪዳን 39 መጻሀፍት ሲኖሩት ፤ አዲስ ኪዳን ደግሞ 27 መጻሀፍት አሉት ። እነዚህ መጻሀፍት የተጻፉት በተለያዩ ሰዎችና በተለያዩ ጊዜያት ነው ። እያንዳንዱ መጽሃፍም የራሱ ስም አለው ። ለምሳሌ ፤ ዘፍጥረት፣ ትንቢተ ኢሳያስ ፣ የዮሀንስ ወንጌል።

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መምጣት ፤ስለሰው ልጆች መሞት መበቀልና ሞትንም ድል አድርጎ መነሳቱን የሚመሰክሩ ደግሞ አራት መጻሀፍት አሉ ። እነዚህም ፤ የማቴዎስ ወንጌል ፤ የማርቆስ ወንጌል የሉቃስ ወንጌል እና የዮሃንስ ወንጌል ናቸው።የእግዚአብሄር አገልጋይ በሆነው በሀዋርያው ጳውሎስ የተጻፉ ደግሞ ብዙ መልእክቶች አሉ። የመልእክቶቹ ስሞች መልእክቶቹ የተጻፈላቸውን አድራሻ ይናገራል። ለምሳሌ ፤ ወደ ሮሜ ሰዎች ሲል ወደ ሮም ወደ ምታባለው ከተማ የተላከ ማለት ነው።

እያንዳንዱ መጽሀፍ ደግሞ በምእራፎች ይከፋፈላል። እያንዳንዱ ምእራፍ ደግሞ በቁጥር ይከፋፈላል ። ለምሳሌ ፤ የሃንስ 3፤1-6 ማለት የዮሃንስ ወንጌል ምእራፍ 3 ከቁጥር 1 እስከ 6 ያለው ቃል ማለት ነው። □